
ይስሃቅ ወርቁ

የወንጀ ጦጣ



http://ethzare.wordpress.com

ምስጋና

- ለዓለሙ ቢያድጌ ጌታሁን
- ለበዛብህ ስሜነህ
- ለኮተቤው የጥበብ ወጌሻ የንታ የሻው ተሰማ
- ሊጋሼ ሥዩም ተፈራ
- ለደራሲ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ
- ለጓጣሚ ለበለው ገበየሁ

መግለቢያ

ከሕይወት ምድጃዬ ጥደት.....የእውነት፣ የሕይወት፣ የውበት፣ የመኖርና ያለመኖር ውህደት እንፋሎት ያሰገነፈለኝን እነሆ:: ከቅስሜ ቅስም፣ ከላቤ ወዝ የነሱ የነፍሴን አብራክ ከፋዮች እነሆ::

እንበለ ዘርዓ ሰብዕ አልተፀነሱም፤ ከህያዋን የዘር ፍሬ በስንኝ የፀነሰኳቸው ናቸው:: በየቀኑ እየተወለደ በየቀኑ እየሞተ ሲድህ ከሚኖር እኔነቴ የተወለዱትን እነዚህን ልጆቼን እነሆ አቆንጁልኝ:: ከልጆቼ መሀል ንፍጥ አፍንጫው ሰር የተለጎደበት ብታግኙ አደራ በምግባር መሀረማችሁ ጥረጉለት እንጂ ንፍጡ የህይወቱ አካል እንዳይደለ ቆጥራችሁ አትጥሉብኝ:: ወይም እንደማናቸውም ፍጡራን (ቆንጆውም ኣስቀያሚውም እንደሚኖር) አስከንፍጣቸው እንዲኖሩ ፍቀዱላቸው:: በር ላይ ቆሜ ብዙ ከማስቆማችሁ ግቡና ልጆቼን እዩአቸው፤ ከምድጃዬ ዳር «ዕርቃናቸውን» አሳቴንና አሳታችሁን እየሞቁ ታገኟቸዋላችሁ:: ግድግዳ አልባ ቤቴን ከፍቼ በጊዜ ግቡ ብያለሁ፤ ግቡልኝ::

ይስማዕከ ወርቁ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

http://ethzare.wordpress.com

መክስተ አርዕስት

አርዕስት	ገጽ
ሕይወት በነጠላ	9
የፈጣሪ አስከሬን	10
ኑ ሞትን ቅመሱ	11
ሳይነጋ	12
ስንፈተ ስብዕ	13
ውርዝው ነጌ	14
የማይከፈት በር	15
ካውያ	16
ፔንግዊን አፍሪካ	17
ጫፍ አልባ ቁልቁለት	19
ባዶ አርጊኝ	20
ሰርዶ	21
ከራስም ሲታነስ	22
ድፍርስርሱ ደሜ	23
ሰሞነኛ	24
ሰይጣን የታደለው	25
ተመየጢ ፈላሲት	27
ዝረፍ ዝረፍ አለኝ	29
ተላለፉ ሲለን	30
አንጋፋው ሱሪዬ	31
አብረን ብንተኛ	32
መንገደ ምርቃና	33
አመክንዮ	34
ፈሶሎጂ	35
ኪርያላይሶን	38
ምነው አምና በሞትኩ	39
እንዲሞቀው በድኔ	40
ይቀረኛል	41
ሲያጋጥም	42

	ገፅ
ልኬታ	43
ሳይቀርቡ ቆርቦ	44
ሰቆቃወ ቂል	45
ሀሳሲ ፈላሲ	46
ዝግመተ ለውጥ	47
የጥጃ ምስል	48
መቅደሴን	49
ይበለኝ	50
ሕልም አልም	51
አዕምራ ለሔዋን	52
ፅንባ ማኪያቶ	54
የግጥም ጅምናዚየም	55
የአፈ ጉባኤው መዶሻ	56
ኩርኩም	57
የገሀነም መዝገብ	58
ሉልነት? ሎሌነት?	59
የትኋን ሽቶ	60
አግቡኝ	61
ጢም አልባ	63
ብርሌ ሲነቃ	64
ልናነጋ ተኛን	65
አያቴ	66
ጉባኤ ፍና	67
ኤዲት ይደረግ	68
ሚዛኑ	69
ከ'ኔ በጥቂቱ	70
አቤቱ	71
ትበጥብህ?	72
ዘመነ መንሱት	73
ስለት	74
የወንድ ምጥ	75

http://ethzare.wordpress.com

ዛሬ ልደቴ ነው፤ ነገም ልደቴ ነው፤ ትናንትም ልደቴ ነበር።።

ሕይወት በነጠላ

አፈር ጥጡን ለቅሞ፣ አባዝቶ....አሳስቶ
በእፍታ ብረቱ፣ አዳምጦ. . . አጥርቶ
በእስትንፋስ ደጋኑ፣ ነድፎ. . . . አሰፋፍቶ
ልቃቂት አልቆ፣ በሀላዊ እንዝርቱ፣ ፈትሎ...አመልምሎ
ሕይወት ነጠላ ነው፤
አምላክ የሸመነው፣ አምላክ ቀጭን ፈትሎ።።
ዘሀውና ማጉ፣ ነው ተመሳቃዩ፤ ኑሮ ጥልፍልፉ።።
ሞት ጥለትም ጌጡ፤
ለኑባሬው ጣዕም ለብኩን ምዕራፉ።።
መጋጠሚያ ውሉ፣ የመሀል ስፌቱ፣ ነጠላ ጥንደቱ፣
ልዩነት ውህደቱ፣ጥበብ አንድነቱ፣ አብሮነት ሐሴቱ፤
የሚንፈራገጠው አልቋጭም ባዩ በዘርፍ ቁጭቱ፣
እምቢ ልኑር ባዩ፣
ነጠላ ቀጭኑ ህይወት ተፈታዩ፣
..... ላ' ንዱ ተዘቅዝቆ፣
..... ለሌላው ሸብርቆ፣
ላ' ንዳንዱ ማሰሻ፣ የመርገምት ጨርቁ
ላንዳንዱ ነጭ ኩታ፣
ድግ ሆኖ 'ምናየው ..... ላ' ንዱ ደግሞ ማቁ፣
ሕይወት ነጠላ ነው፤
አምላክ ቀጭን ፈትሎ፣ አምላክ የሸመነው፤
ሞገሱና ዕድሜው ግን፣ እንደ ለባሹ ነው ።።

http://ethzare.wordpress.com

ሳይነጋ

ይህን ወረቀት 'ማበላሸው
በብዕሬ እንባ 'ማቆሸሸው
ሳይነጋ የወለድኩት ልጅ
ክሴን እንዳይጥፍበት ነው።

ስንፈተ ሰብዕ

የተኛ በቆሎ ጎርፍ የደፈጠጠው'
ተኝቶ ያፈራል ትል እያላመጠው።
ድንጋዩን ሳይሜን አፈሩን ሰይለብሰው'
መፈርጠጡስ ይቅር፣ መዳህ ያቅተዋል ሰው!?

http://ethzare.wordpress.com

ውርዝው ነጌ

የዝሆን አዳኞች፣ ዛፉን አከርክረው ይቀቡታል ጭቃ።
አንዱ አቢይ ነጌ
የዝሆን አሮጌ
ሲደገፍ እንዲወድቅ ከዛፉ እንዳይነቃ።
አበይት ነጌያት - - - ይሰበሰቡና
ሊያነሱት ሲያቅታቸው
በኩምቢያቸው ገፍተው
ጩኸት ያሰማሉ
ውርዝው ነጌ ይምጣ ያንሳልን አያሉ።
ውርዝው ነጌ መጥቶ- - -
በጠንካራ ኩምቢው በኃይሉ ተገፍቶ
የወደቀው ዝሆን ይነሳል በርትቶ።
የታል የኛ ዝሆን የኛ ወጣት ነጌ
ተደግፈን ስንወድቅ ስንሆን አሮጌ
ገፍቶ የሚያስነሳን የኛ ውርዝውሳ?
አንደ መቅደላው ፈርጥ አንደ ቋራው ካሳ
ኢትዮጵያዊ ነጌ ምናለ ቢነሳ?

የማይከፈት በር

ለግቶ - - - ፈክቶ - - ሐቆ
ለክሮ- - - መሽቶ- - - ባርቆ
ተምዘግዝጉ - - - ወድቆ
ተንገዳግዶ - - - ደቆ
ዞሮ- - - ናላ አዙሮ
በውሉደ ጌሾ - - - በጥንስሶች ለክሮ
ቤቴ ካሳት ጎጆው - - - ከበር ተትሮ
አይከፈትልህ ሲለው ለሰካራም
ግድግዳውን አንጂ በሩን አያንኳኳም።

http://ethzare.wordpress.com

ካውያ

ካውያ ቢኖረው ለስው እንደሱሪው እንደልብሱ
ሲጨማደድ ቀጭን ቆዳው ሲጨማተር ገበር ነፍሱ
ካውያ ቢኖረው ለስው ካውያ ቢኖረው ለ'ሱ
የአያቶቹን ገፅ የአያቶቹን ገላ ቢተኩሰው በታደሱ::



ፔንግዊን አፍሪካ

ኦ እናት ፔንግዊን ኦ እናት አፍሪካ ፀሊም ወፀአዳ
የእኔነቴ ማጀት የእኔነቴ ጓዳ
ጀርባሽ ጥቁር ካባ ፊትሽ ነጭ ጋቢ
በማያበር ክንፍ ሁሌ ተርገብጋቢ
ለሆድሽ ደመኛ ለእኔ ተንገብጋቢ::
ሆድሽን አያማረው ጦመሽ ለእኔ አጥጋቢ::
ጠግቤአለሁና ከአፍሽ በተከካ
ከአፍሽ በተቦካ
አድጌአለሁና ከአፍሽ በተከካ

http://ethzare.wordpress.com

ከአፍሽ በተቦካ

አ ለናት ፔንግዊን አ እናት አፍሪካ
አንቺ የፍቅር አምባ አንቺ የእናት ዲካ
የመቀበል ንፉግ የመስጠት ቋርፍ ዋርካ
ከኢምንት ውቅያኖስ የኔ ቅድመ ሕዋስ የሕላዌ ባርካ
መብረር አስተምሪኝ ይህን ፍቅር ልስበክ ከአውሮጳ-አፍሪካ::
አ እናት ፔንግዊን አ እናት አፍሪካ
ዋካ- - ዋርካ - - ዋካ
የነጭና ጥቁር የአንድነት ሰንደቅ
የእርግብ እና ቁራ ቅኔ ሰምና ወርቅ
ካባ እንደ ደረበ የአቋቋም መርጌታ ምላሌሽ ከመሊቅ
የነጭና ጥቁር የእርቃችን ሰንደቅ
ሁኚ ሐሳዊው ነጩ ርግብ ይልቀቅ::
አ እናት ፔንግዊን እንደ ገዴ አሞራ ፀሊም ወፀአዳ
ከአፍሽ የተከካው ነው እንዴ የኔ አዳ?
አ እናት ፔንግዊን ከማሁ ለገዴ
አ እናት አፍሪካ አንቺ እናት ዓለም
ነፃ ስጠታ እንጂ ፍቅር ዕዳ አይደለም
የሚሰጥ እጅ እንጂ ፍቅር ኪስ የለውም::
አ እናት ፔንግዊን
አ እናት አፍሪካ ቅኔሁ ለዳርዊን
ዕዳ አይደለም እንጂ ፍቅርሽ ዕዳ ቢሆን
ትቼው ረስቼው የዕዳ መዝገቡን
ከፅንስ አስከ ልደት ሁልቆ መሳፍርቱን
የተቢደርኩትን የተበደሩቱን
መች በቻልኩ አከፍልሽ ያኔ ለቋቋሽኝ የእንቁላል ቅርፊቱን!?
አ እናት ፔንግዊን አ እናት አፍሪካ
አንቺ እናት አለም ጥቁሯ አንታርቲካ
ኤሊዎች ቀደሙሽ ድክድክ ስትይ ላትይዥ ስታደቢ
እግሮችሽ አጠሩ
ከንፎችሽ ገረሩ
ጎንበስ ቀና ስትይ በሆድሽ ሰብስበሽ ለበይ ልታጠግቢ
ኤሊዎች ቀደሙሽ በማያበር ክንፍ ስትርገበገቢ::

ጫፍ አልባ ቁልቁለት

የያዙትን ይዞ ካልተንጠላጠሉ
ወደ ላይ ካላሉ
ወ
ደ
ታ
ች

አ
ያ
ይ
መውደቂያን ካስሉ
ከውድቀት ዳርዳሩ ከተንደረደሩ
መውደቅ ከጀመሩ
ውድቀት ጫፍ የለውም
ሜዳው ቁልቁለት ነው ውድቀት ዳር የለውም
በውድቀት ላይ ውድቀት አየተያያዘ እየተዋዋለ
ከውድቀትም በታች ሌላ ውድቀት አለ::

http://ethzare.wordpress.com

ባዶ አርጊኝ

ከንፈርሽን ልጉረስው ላ'ንዴ ከንፈሬን ግመጪው ላ'ፍታ::
በእቶን እስትንፋስሽ ቅጥለት ይትነን የወስጤ አንድምታ::
የቆመው ኩሬ እምነቴ
የወየበው ፍልስፍናዬ
የወረዛው እኔነቴ - - ይድረቅ አንግዴህ ልጣድ፤
አሙቂኝ አንቀልቅይኝ በይ አንድጅኝ በጭንሽ ነዲድ::
አዳውሪኝ ይበጥበጥ ውስጤ፤
ብቀይ ባህር- ሸሸ ላይ ተጫወች በልቤ ካርታ፤
ሠውሪኝ በገነትሽ ሥር ባዶ አርጊኝ እስኪ ላ'ንዳፍታ::
በዛብኝ እኮ እግዚኦታ!
ይኸው ሶስት ሺ ሃሌታ፤
ይኸው ሶስት ሺ ኡኡታ፤
ጥበብ መቀነትሽን ፍቺ አስረሽኝ እስቲ ላ'ንዳፍታ፤
በአንዲት የፍቅር
ጠ
ብ
ታ
::



ሰርዶ

ድርቁን - - - ጉንቁሎ
- - ሳይተክሉት - - - በቃቅሎ
ፅድቁን ሲከለል - - - ይብሱቱን – መንግሎ
አረንጓዴ 'ሚሆን - - - ሲጫኑት – ሥር-ሰዶ
ወደ ሥር - የሚያድግ - - - ከላይ ሸክሙ ከብዶ
በተጫኑት ቁጥር በታረቁበት ልክ - - -
ሥሩ 'ሚለመልም- - በሥራ ሥር እጁ - - መሬቱን ጨምድዶ
ድንጋዩን - - ፈን- ቅሎ ቢጫነቱን - ጥሎ
ሲቆርጡት ጎንቁሎ - - - ሲጫኑት ሥር ሰዶ
ቀዩን ቀጥኖ - 'ሚያብብ - - ሸለፈቱን ቀዶ
ሰርዶ እኮ - ጀገና ነው
ጀግና እኮ - ነው ሰርዶ::

http://ethzare.wordpress.com

ከራስም ሲታነስ

የግዙፎች ጥላ - ሲያጠላ
አልፍ ነጭ ጥላ - ጥቁር ጥላ::
ከፀሐይ ብርሃን - ሲያጣላ
ከመወየብ ዛፎቹ ስር
ከ...ሥ...ር
ከራስም ከማነስ እኮ
ታኮ
ተጠምጥሞ ወጥቶ በመደግደግ
በጥግ
መሆንም እኮ ደግ
እንደ ሐረግ::
ከብርሃን አብሮ ተቃምሶ
የራስ መቁነን ለመፈለግ
ከመዋየብ ከመጠውለግ
አዛፉ ሥር
አዛፉ ጥግ
ተጠምጥሞም ተጠማዞም
ከላይ ወጥቶ ለመጠገግ::
መሆንም እኮ ደግ
እንደ ሐረግ::

ድፍርስርሱ ደሜ

አንቺስ እቴ በየወሩ
ሲያጥጥሽ ፍሬ ዘሩ
ያበጠ ማህፀንሽ ግድግዳው
ደምሽ የወጣጠረው
ቀይ ስጋሻሽ ቀይ እንግዳው
ቀይ አበባሽ ቀይ ፍሬው
አበቅቴሽን ያልዘነጋው
የወር ቁጣሽ ሲወጋጋው
የጠወለገው በድርቅሽ አቶንሽ ያንቀለቀለው
ነግሎ ይወጣልሻል አጥትሽ ሲመነግለው::
ይብላኝ ለኔ ይብላኝ ከቶ
ስቃጠል ለምኖረው ድፍርስርሱ ደሜ መውጫ አጥቶ::

http://ethzare.wordpress.com

ሰምነኛ

በሌለ ቅዳሴ ስሞነኛ በዝቶ ስንዴ እንዲወረዛ
እንደ ዘኬ ቆሎ ዝና እየተነዛ
ትናንት የጉድ ተብሎ ለዛሬ ጠነዛ
ማታ ተድመንምኖ ጧት ሆነብን ጤዛ::
ፅዋ እንደሚረከብ ያቦ ባለተራ
እንዳፈረሰ ቄስ የፅጌ ደብተራ
ስም ሰሞነኛ ነው ገኖ ፣ሚሆን ተራ::

ሰይጣን የታደለው

ሰይጣን የታደለው!
ሱሪው አያልቅበት፤ እህል አይቸግረው::
- - - -አይበርደው፤ አይሞቀው::
ሰይጣን የታደለው!
- - - ቀድሞ ቁርጥ ያወቀው
- - - እፀድቅ - እኮነን ሲል የማይጨነቀው
ሰይጣን የታደለው!
- - - ልጁ አያለቅስበት፤ ሚስቱ ልፍታ አትለው
ሰይጣን የታደለው!
- - - ሱሱ ፣ማይደቁሰው
- - - ጎጆ ፣ማይቀልሰው
- - - አፈቀርኩ ብሎ
- - - አንገት ማይደፋው
- - - ወሲብ ቅንዝርና ቂም ማያዳፋው
- - - የማያርስ የማይጎርስ የማይጎለጉለው
ሰይጣን የታደለው!
- - - የስልጣኔ አባት
- - - መፈንቅለ መንግሥት
- - - ቀድሞ ያካሄደው
ከሰው ልጅም በላይ፤ ፈጣሪን የሚያውቀው
የፈጣሪን ምስጢር፤ አክስሎ የሞቀው
ባለውለታችን፤ ሊቁ መልአክ ሰይጣን፤ ከበለስ ጀምሮ
የተፈጥሮን ምስጢር፤ ያምላክን ቋጠሮ
ለሰው አቀብሎ፤ ለሰው አንቆርቁሮ
ፈትኖ ፈታትኖ፤
ቀድሞ ተፈታትኖ፤
ሰውን ሰው ያረገው
ግልፁ ደግ መልአክ ሰይጣን የታደለው!
ጥርቅምቅሞሽ እምነት ተደፋ! ተወጋ! ወደ ጥልቁ ውረድ!
- - - ሲለው የማይፈራዉ

http://ethzare.wordpress.com

- - - እኔ ላይ ተባሮ አሷ ላይ 'ሚሰፍረው
- - - ሙስሊም ክርስቲያኑ - ጴንጤ ኦርቶዶክሱ
- - - ካቶሊክ - - -ዊትነሱ - ምዕመን መናፍቁ
- - - ባለዛር ጠንቋዩ - - ድፍን ቅሉ ሲቁ
አስወጣሁት ሲለው ምንም የማይመስለው
ሳጥናኤል ታጋሹ ሰይጣን የታደለው
ሳጥናኤል ሉሲፈር ፀሎት አያደቀው ውዳሴ አያደምቀው
ጨለማ አይዘፍቀው ገነት አትናፍቀው::
ሳጥናኤል ሉሲፈር ፍቅር የራበውን
ከልቤ ጠሊቅ ሥር ምናለ ብወደዉ
ጠላቴ ከሆነ - - ሰይጣን ወዳጀ ነው::
አስኪ በዚህች እንኳ ታላቁን ልብለጠው
ልጁ ሲያስተምረን - ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ ነው::
ምነዋ ይህች ቃል ለ'ሱም የማትሰራው?
መቂያቂያም በቂም ልክ ቂሙን ቢደብቀው
ምነው የእሱን ሥራ የማይታረቀው?
ለሰው ልጅ ተሰቅሎ እጥፍ ለበደለው
ምነዋ ወዳጁን ይቅር ይብቃ ቢለው!?

ꕥ ꕥ ꕥ
(ለክርስቶስ ሰምራ፣ ወለዘይገርም ፍልስፍና ዘፎገራ)

ተመየጢ ፈላሲት

ይድረስ ለፈላሻዋ- እነሆ እኔ ሐበሻው ነኝ
ቅድመ ፍልስት- ቅድመ ክህደት ከፍቅርሽ ገፈት ያቀመስሽኝ::
ፈላሻዋ ፍቅሬ ጌጤ የእምዬ ልጅ የእናቴ
በውኑ ልብሽ ቆርጦ ክዷታል- እማማ ኢትዮጵያን በሞቴ?
በለጋ ልቤ ያጠበቅሽው የፍቅር ፈትልሽ ቁርኝቱ
ጠብቆብኝ የፍቅርሽ - ፍቅሬ ክረቱ
ደግመሽ በፈለስሽበት ምድር- አስራኤልን በመላ አሰስኩ::
"አመሐልኩክን" ብዬ የኢየሩሳሌምን ቆነጃጅት ጠየኩ::
ቴልአቪቭ- ጎልጎታ ሳስፈልግሽ ስፈልግ ኖርኩ::
በናዝሬትም-በገሊላም-ፈልጌ አስፈልጌሽ ነበር:
በኢዝራኤል ሸለቆ አድባር- በሞርያም ተራራ ሥር
በዶር ሱልጣን በር ሁሉ ፈልጌ አስፈልጌሽ ነበር::
ግን እስኪ ልጠይቅሽ ያጣሁሽ ፈላሻዋ ፍቅሬ
ድህነት ኢዘለአለማዊ መሆኑ አልገባሽም እስከዛሬ?
ክደሽ የተውሻት ምድር- እምዬ ኢትዮጵያም
ደሀ አሮጊት ብትሆን እንጂ- በእናትነት አትታማም::
ጥበበኛ እጅሽ ይመስክር - ስንዴዋን ለብርሃንታሽ የጋገረው
አለቷን ለምኩራብሽ የፈለጠው - ዋልካዋን ለሸክላሽ የቆፈረው
እስኪ ከናዝሬት- ገሊላ በተመላለሰው ጌታ - አንዴ ልጠይቅሽ ፍቀጂ?
ነፍስሽ ከላይ ከራማ
ስጋሽም ከአማማ ኢትዮጵያ አውድማ የተቦካ እንጂ
እስኪ ስለ እውነት መስክሪ - መሬቷን የሳምሻት አስራኤል
ሆነችልሽ አናት አገር?
ያቺ አማማ ያለበለችሽን ቀሚስ ያቃጠልሽባት ከነዓን
የምታፈሰው ደም ነው ማር?
ያንቺም ቢሆን ያ ያፈቀርኩት ገላሽ ጥቁሩ
የፍጥረት መቅድምሽ ሥሩ - ጥቁር አይደል ፍሬ ዘሩ?
እስኪ በፈጨሽው ጥቁር አፈር - በቀዳሽው ጥር ምንጭ ማይ
ሥጋዬ የተከመረው አጥንቱ የለመለመው ከአማማ ኢትዮጵያ ጤፍ
ዳጉሳ አይደለም በይ?
አንደ ጣና ሳቢላ በረሽ የሰፈርሽባት ከነአን

http://ethzare.wordpress.com

መቼም ጊዜ ደግ ነው ያደረገችውን ሰማን::
ተንቆረቆረ አሉ ደምሽ ቀድታ ፈትሻ ደፋችው
የእኔ አይደለሽም አለችሽ- ይኸው ቁርጡን አወቅሽው::
አንቺ ፍቅሬ ፈላሻዋ መቼም እናትሽ ኢትዮጵያ
ከርዛት ርሃቧ በቀር ላላር ነው መቼም ላላር
እናትነት ከሷ ወዲያ
የግላንግሉ መጠጊያ- እናትነቷስ የጉድ ነው ኢትዮጵያ
ለእምነትሽ - ምኩራቧን ለፍቅርሽ ወጣቷን ሰጥታ -
እኔን ልጇን ለግላሽ
እናታለም ኢትዮጵያ ከአላት ከቶ ምን ነላችሽ?
ነይ ተመለሽ ስሞትልሽ::

ዝረፍ ዝረፍ አለኝ

ሽርክተው ሆዱ ላይ
ይጎልጎል አንጀቱ ህብር ቅኔነቱ
ይበጥበጥ ሃሞቱ::
ፊኛውን ሸንትረው
ይንቆርቆር በሆዱ ምስጢር ውል አንቀፁ
የማያልቅ ሽንቱ::
ባዶነቱን ፈትሽ ገቢር ተገብሮውን ከሱሪ ከኮቱ::
ማንደርደሪያው ድረስ ይሩጥ እስከ ቤቱ::
ያንተ ነው የኪሱ ያንተ ነው ጥሪቱ::
ከምስጢሩ ስበር ከጉልጥምቱ መቅኔ፤
ዝረፍ ዝረፍ አለኝ
ንጠቅ ንጠቅ አለኝ የየኔታን ቅኔ::



http://ethzare.wordpress.com

ተላለፉ ሲለን

ከመረዋው ውግረት ከቃጭሉ ዋይታ እኩል ብንሰማም
በአንድ ደወል ድምፅ ግለ ህሊናችን አንድ ላይ ቢደቃም
ተላለፉ ሲለን ፊትና ኋላ እንጂ እኩል አንነቃም::



አንጋፋው ሱሪዬ

አባቴ አንድ ሱሪ አለው - ጥንት አባቱ ያወረሰው
ጠቦት ጠባቦት ያ'ኖረው::
«ልበሰው» አለኝ ሱሪውን - ብለብሰው ሰፋኝ- ሰፋፋኝ::
በሱሪው ውስጥ ቅማል የሆንኩ ያህል ሰፋኝ
ምዕት ጊዜ አስጠበብኩት - - ምዕት ጊዜ ሱሪው ሰፋኝ::
አልፍ ጊዜ ባስጠብበው - - አልፍ ጊዜ ጠባበበኝ
ለሱሪው ግመል ብሆንም አየጠበበኝ ለበስኩት - - -
ሱሪዬ ለብሶኝ ታጠኩት::
መቀመጫዬ ላይ ላ'ሳር ሱሪዬ በታች ፈነዳ
ወሽመጥ አስገባሁለት መጣፊያው አገባኝ ዕዳ::
ያ'ባቴን ሱሪ አወለኩት
አኔም ለልጄ አስቀመጥኩት::



http://ethzare.wordpress.com

አብረን ብንተኛ

ና- - - አብረን እንቆፍር አብረን እንማስን
ና- - - አብረን እንዝራ አብረን እንበትን
ና- - - አብረን እንተኛ እንጋራ አንድ አልጋ
ጀንበሯን ቀስቅሰን አንድ ሌት እናንጋ
አብረን ብንተኛ መደብ ባንለያይም
የራሴን ህልም እንጂ ያንተን ህልም አላይም::



መንገደ ምርቃና

መሄድ ከተቻለ ሂዱ ሌላ አስሱ ከወዲያኛው አለም
ምጠቁ ጥለቁ ይቅናችሁ ግድ የለም::
ምጠቁ ጥለቁ በጉም ሃሳብ ሕዋ በምርቅንቅን ዓለም::
. . . ግን. . .
ያክር ሲበጠስ
ሲከጅል መመለስ
ምርቃናው ሲለበር
እውነት ሲበረበር - -
ማንነት ሲቀለም
በፍናተ ቅዠት በምርቅንቅን አለም
ወላጅ መንገድ እንጂ መላሽ መንገድ የለም::



http://ethzare.wordpress.com

አመክንዮ

ለምን ፈጠረኝ?ትላለህ፤
ለምን፤ሞታለሁ?ትላለህ
ዝም ብለህ መኖርክን ትተህ
ዝም ብለህ መሞትክን ትተህ
ለምን ኖርኩ? ለምን ሞትኩ?
እንዴት? ኢያለ
ሳምጭው ለወላጁ አንጋጠ
ሕሊናህ ለምን ማለለ?
በመኖር ያለመኖር ጫፍ
አመክንዮ ቀድሞስ መች አለ!?



ፈሶሎጂ

እሰይ! ፈሳሁ!
ሐሹ! ፈሳሁ!
በቃ! ፈሳሁ!
አስተንፋሽ ቦታ ሲጠፋ ለካስ ፈስም መድኃኒት ነው::
የላይኛው ሲከለክል ልሳን ሳንቃው ሲከስም
ለካስ እንዲህ መድኃኒት ነው በታችኛው መተንፈስም::
የሆድ ብሶት ጉርምርምታ - የህሊና እቦጥ እምቢልታ
ትንቅንቅ ውስጤ ሲመታ - እፍ ሲሉረቸም በቃታ
ምናለ በታች ብፈታ!?
በፈስ አብዮት ድምታ - የማንስ እገር ተፈታ?
ወገኔ ባክህ ተጠየቅ - ፈስ ነፃ ፈቃድ ነው?
ወይስ የሽንት መንቆርቆር ማጀቢያ የቄጤቱው ሙዚቃ ነው?
የላይኛው ሲከለከል ምናለ ትንሽ ብንፈታ
ባሕር ማዶ እኮ ወገኔ አፍ ተከፋፍቶ ተንሳ
እግር ተነስቶ ተፈሳ::
አምቂ ተጠርንቁ አልሞትም እኔስ አጪስዋለሁ!
ድርግም! አድርጌ እፈላለሁ
ሆዴ እስኪሰላ ድረስ ድብን! አድርጌ እፈላለሁ::
ሰው በሌላም ይዋረዳል ለመዋረዱም ግዴለም
ፈስ የያዘን ማጭበሪያ እንጂ የታየን መስዋዕት አይደለም::
ውጊያውን እንጀት ተንከሶ አጅሬ ቁልቁል ሲረግጠው
መቋጠሪያዬ ሽምቀቁን ክዳር ዕዳር ሲያጠብቀው
እንደ ማታ ጎለል ሽብሸቦ በጅማት መቀነትነት ሽንሸጉን ሲጠረንቀው
እንደ ሴጌምን ሹብዳ ከላይ ኢታች ሲያጣድፈው
ሆዴን ሽትብ ገልብጦ እግሬን ሲያንከረፍፈው
ከርሴ ውስጡ ሲጻምን ከበሮ ሲያክል ተነፍቶ
በልቶት አትልቶት ትግል ደመና ሲዞር አስፋፍቶ

http://ethzare.wordpress.com

የሐምሌን ሰማይ አድርጎት ሆዴ «ድም»... «ግም»... ሲል
ሆዴ የነሐሴ ኩሬ ሆኖ እንዳፈቀረ እንቁራሪት
ቁርር . . . ቁርር . . . ጩርር . . . ጊጭ ሲል
እንደጧት የኪዳን ደወል ከላይ አታች ሳቃጭል
ነጭ ላብ ፊቴን ሲያጠምቀው ሽምቀቅ . . ጭንቅ . ድቅቅ . .
ፉቅቅ . . . ጥምቅ . . . ጥልቅ ድብቅ ሲያደርገኝ
ከንፈሬን ስጨረግደው
ወገን ታዲያ ምናለ ምጤን ብገላገለው?
ድምፁ እንዳይረብሽ አድርጌ ከቋጠሮው በስስ ብፈታው?
መቼም ነፃነት በራበው ምድር «ዘረጥን» ቀድሞም አላውቀው
እንዴው በትንሽ በትንሹ ኡ-ሱ-ሱ-ሱ . . . እንጂ በየደቂቃው
ነገር እንዳይበላሽ ድምፁ ከመ መብረቅ ባርቆ
ያኔ ጥግ ከአድማስ ባሻገር ርቆ
ይሉኝታ ደንበር ተሻግሮ ሀፍረት በቁም ሲረታ
አቤት ያለው የደስደስ አቤት ያለው እፎይታ
የታችኛው ወናፍ ሽምቀቅ ቋጠሮ ውሉ ሲፈታ
አቤት ያለው የደስደስ አቤት ያለው እፎይታ!!
ወገን ታዲያ ምናለ
ያበጠ ጥቁር ሆድ ሁላ ከዚህች ምድረ አፍሪካ
የተነፋ ቀበተት ሁላ ከዚህች ምድረ እንካ ለእንካ
በእከክኝ ልከክህ ታክቲክ ባጉርሰኝ ላጉርስህ ዳካ
በሆድ አብዮት ገፈጠጥ የተነፋ ክርስ ሁላ በተቦካ ባልተቦካ
ወይም በሆድ አብዮት «ሆዱ ካገሩ የሰፋ»
«መድኃኔአለም ያጥብልንና» ሆዱ ካገሩ ሰፍቶበት
የጎረቤት ወሰን የገፋ
ወይም . . . በብግነት ድማሚት ሆዱ
ጥልቀት ላዕሉ የተነካ
በእከክኝ ልከክህ ታክቲክ ባጉርሰኝ ላጉርስህ ዳካ
በሆድ አብዮት ገፈጠጥ የተነፋ ክርስ ሁላ በተቦካ ባልተቦካ
ወይም በሆድ አብዮት «ሆዱ ካገሩ የሰፋ»
«መድኃኔአለም ያጥብልንና» ሆዱ ካገሩ ሰፍቶበት
የጎረቤት ወሰን የገፋ
ወይም . . . በብግነት ድማሚት ሆዱ
ጥልቀት ላዕሉ የተነካ
ምናለበት ቢተነፍስ በእ-ሱ-ሱ-ሱ . . . ድምፅ አየለካ::
የላይኛው በር ሲዘጋ
በታችኛው መተንፈሻም መድኃኒት ነው አቴ-ለካ!!

ሐሹ! ፈሳሁ
አሰይ! ፈሳሁ
አራስ ብሎ ሚጠይቀኝ እንደማይኖር አስቀድሜ አውቀዋለሁ::
መቸም በሀገራችን ትውፊት ልማድ እስከ ዛሬ እንደማውቀው
ለፈስ አራስ መጠየቂያ ሳቅ ወንቀት ደብልቅ ነው::
. . . . ግን እኮ . . . .
ቋጠሮ ውሉ ጠብቆበት በሩፋኤል ፀሎት ላማጠው
ከጭንጋፍ ልጅ ልደት ይልቅ ወደል ፈስ እኮ ግልግል ነው::
የከንቱ ልጅ ምጥንና የፈስ ምጥን ሚለያቸው
ከንቱ ልጅ ወደውጭ ቁልቁል ፈስ ወደ ውስጥ መማጡ ነው::
ፈስ ማለት እኮ ወገኔ
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ለአያ አዝብጤ መንገድ አቅኚው
የመጥምቁ ተምሳሌት ነው::
ፈስ ማለት እኮ ወገኔ
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ከልዒቅ እስከደቂቅ በሀቡዕ የሚያብላላው
ለዘመናት ያልተጠና ኑክሊየር ኢነርጂ እኮ ነው::
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ለአህያ መደንግፀ-ጅብ
ለውሻ-የጩኸቱ አጀብ
የህልውናው ቃጭል ነው
ሌሊት አዳሜ ሲያሸልብ::
ሐሹ ! ፈሳሁ
አሰይ ! ፈሳሁ
አንኳን! ፈሳሁ::
አስተንፋሽ ገደል ሲጠፋ ለካስ ፈስም መድኃኒት ነው::
የላይኛው ሲከለከል ልሳን ሳንቃው ሲከስም
ለካስ አንዲህ መድኃኒት ነው በታችኛው መተንፈስም::
የሆድ ብሶት ጉርምርምታ - የህሊና እበጥ እምቢልታ
ትንቅንቅ ውስጤ ሲመታ - ልሳን ሲቆለፍ በቃታ
ምናለ በታች ብፈታ!?
በፈስ አብዮት ድምታ የማንስ አገር ተፈታ? ÷
መቼም ነፃነት በጠማው ምድር «ዘረጥን» ቀድሞም አለውቀው
አንዴው በትንሽ በትንሹ ምናለ ፈሴን ብለቀው?

http://ethzare.wordpress.com

ኪርያላይሶን

ታአስ ናይናይ ኪርያላይሶን
ትስቡጣ ናይናይ ኪርያላይሶን
አዶኒ ናይ ናይ
ኣያልኩ ቆሜ ስፀልይ
ፍላጐቴን ቃሏን ገድፌ
ጥያቄ እንቡጧን ቀጥፌ
ኑኡታ አይኖቿን ጠቅቼ
በአርምሞ ቀጭን መርፌ
መሻቷን ውስጤ ቆልፌ ተማፅኖዋን ገርፌ
በግለቷ ውኃ ከልሼ
ቅዝቃዜዋን አምሼ
ውስጤን ራሴን የወጋሁ
በኪርያላይሶን አንካሴ
«አምባገነን» የምል ሌላውን
አምባገነን ነኝ የራሴ።

ምነው አምና በሞትኩ

እከከከከ . . .! አህህህህ. . !
. . . አበስኩ . . ገበርኩ . .
ምነው አምና በሞትኩ!
ብጣቂ መሬቴ ወስደው ሳይተኙባት!
መቃብሬን ሠርቀው ሳይቀበሩባት!
አህህህህ. . .! አበስኩ ገበርኩ!
ምነው አምና በሞትኩ!

(ኦ ሔዋን መሬት አንቲ)

http://ethzare.wordpress.com

እንዲሞቀው በድኔ

ጥጤ ዛፌ ጥጤ
ጥ...ቁ...ሩ...ን... ዘርቼ ያበቀልኩሽ ጥጤ
ውሃ የደፋልሽ ያረመሽ ጣቴ
ሊያባዝትሽ መጣ ለባዳ አከላቴ::
መሆንሽን ቢያውቅማ የውስጥ ከፈኑ
ቢያወጥርሽ እንጂ እንዲሞቀው በድኑ
መች ያሳሳሽ ነበር ያኔ በቀጭኑ::



ይቀረኛል

ጉጀዬን ልሠራ ሐረግ ስመዝ ኖሬ
ማገር ሰቆርጥላት የትም ዞሬ ዞሬ
ራሴን ልችል ነው እያልኩ ከችግር
ቆላ - ደጋ ስግር
ለካስ ይቀረኛል አብሮ የሚያማግር
ውሃ የሚያቃጥን ተስፋ የሚያጋግር::

http://ethzare.wordpress.com

ሲያጋጥም

ልቤ በግኖ ነዶ ራሴን በፎከትኩት
ሌላኛ ጠላቴን ቅማሌን ገደልኩት።

ልኬታ

እናቶቻችሁን ለኩ - - እኔም እናቴን ልለካ።
የፍጥርጥሬ ውል ሥሩ ዘረመሌ ውስጧ ሲቦካ
«እም» ብላ አግተምትማ
እህ ብላ ንጣኛለች ለካ።
- - -ለካ እንዲህ ነው ለካ- - -
ገንፍዬ ያቆሸሸኳትን አረፋ በፍትወቷ አቦል በረካ
የግብረ ሥጋዋን ጨምገኒት የቅንዝርዝር ምንዝሯን ሳንካ
«ልጄ» አለች እንጂ ለምዶባት ህጋዊ ውርጃዋ ነኝ ለካ።
ትውልድ እናትክን አስለካ
ትውልድ አባትክን ተለካ
ፍጡር ነኝ ያለ ሰብአዊ ክእናት ከአባቱ ሲከካ
ስንቱ ነው የተወለደ ስንቱ ተጠርቶ ነው የፈካ?

http://ethzare.wordpress.com

ሳይቀርቡ ቆርቦ

ማወቅስ ቀድሞ ነበረ ቀስ በቀስ
ቀርቦ ብልልቶቹን መቃመስ::
በፍቅር ልቡን አብሮ ሆድ ምጣድ ቀጨን ማባለት
በባረ ውስጡ መቀባት::
ሀሳብ ቁጢቱን መቋጨት
ማወቅስ ቀድም ነበረ አውቀት
- - - አሁን ግን- - - -
ከንቱ ወበከንቱ ነው ቂስ ቆሞሱን መወቃቀስ::
ከንቱ ወበከንቱ ነው ሳይቀርቡ ቆርቦ ማለቃቀስ
መቼስ የላይኛው ካልቸረ ቁርኝቱ የማይበጠስ
«አጭ አማጩ» በምን ያውቃል ሰው በማንኪያ አይቀመስ::

ሰቆቃወ ቂል

.....እናም
መውደዴን ባልነግርሽ ሆኜ ጦረቀናም
እኔ በአንቺ አልቀናም::
ይሥረግረግ ያንቺ ሠርግ ይደስደስ ያንቺ ዳስ::
ዳስሽ ተደስድሶ ባልሽ ተመርቆ
ልቁጠር እንደ ዘመድ ሰባራ ብርጭቆ::
አልፍ አለላፍ ውሻ በአጥንት ሲጣላ
ከጓሮአችሁ ቆሜ ይሽተተኝ አተላ::
ጥንብ አንሳ ይኩሳብኝ ከሥጋችሁ ሰርቆ::
ይሽተተኝ በጓሮ ፈርሱ ከጥንብ ልቆ::
ሳልፍ በደጃቸው በፈረሰው ዳስሽ
«ና ቅራሪ ጠጣ» ይበሉኝ እናትሽ::
ክላምንት በኋላ ከተደፋ አተላ
ሚዜው ዕቃ ረስቶ ጠፍቶ ተላላኪ
ይላኩኝ እናትሽ ልበል «ሰላም ለኪ»::
የሌላ መሆንሽ ፍፁም ተረጋግጦ
ልቤ በደም ጠልቆ ጨቅይቶ በሽቅጦ
ኮስምኜ ኮስምኜ እንደ አባቴ ጥጃ
ከጓሮሽ ቀብረውኝ ይብቀልብኝ ሙጃ::
ለቂል አይኔ አርጥባን የልቤ ውስጥ ዳጎን
ነይ ላውስሽ ጥፍሬን ኣክኪበት ባልሽን::

http://ethzare.wordpress.com

ሀሳሲ ፈላሲ

የጥበብ ቤት ጠፍቶኝ አሰስኩ ሜዳ ሰርጡን
ለፈ ወለፈ አያልኩ የብብቴን ላላይ የቆጡን የባጡን
በስንቅ አልባ ፍልሰት ያጣሁት ላስለው
ለካስ ጥጌ ኖሯል ቀድሞ ሲቀልሰው::

ዝግመተ ለውጥ

ከማህፀን ዱድያሌብ የሰው ልጅ ቀድሞ ሲፈጠር
በልሙጥ ጥፍጥፍ ፊቱ ላይ አፍንጫ የለውም ነበር::
ከሰመመኑ ሲነቃ አያትና በገነቱ በር
ከአጥንቱ ገመገም አድባር
የሰረቀችውን ጀምበር
በፍቅሯ ጨረር ስትወጋጋው ዕንባውን አንቆረቆረ::
በእንባው ድንገተኛ ጎርፍ ልሙጥ ፊቱን ሸረሸረ፤
ፀሐይዋ ስትጠልቅበት ወደ ምዕራቧ በረረ፤
በእንባው ፊቱን ቆፈረ፤
በሁለቱ አይኖቹ አንባ ሁለት ሸለቆ ፈጠረ፤
በሁለቱ ሸለቆ መሀል ትንሽ ተራራ ቆለለ፤
ዕንባውን የሚምግበት ሁለት ቀዳዳ ነደለ፤
ስለተራራው ስያሜ ማንም ምንም አላለ፤
አስቀድሞ እሱ ራሱ «አፍንጫ» ስላስባለ::



http://ethzare.wordpress.com

የጥጃ ምስል

አወይ ላምዋ
ተ ላ ላ ዋ
አርግዛ አሳት - አምጣ አሳት
ወልዳ በዱር - አዛፉ ስር
ጅማት ነገር ውትርትር
ቢሞትባት ላትጠግበው ቆዳውን ገፈው አውጥተው
ሥጋውን በገለባ ሰግተው አጥንቱን በእንጨት አጥንተው
ታ ም ቆ - ተ ጠ ር ን ቆ
ምስለ ጥጃ ሕይወት አልባ
አፅመ አንጨት ወገለባ
ከጡትዋ ስር ተሸጉጦ
ላያስወርድ ልጎ ንጦ
አወይ ላምዋ ተላላዋ
አለ መስሏት እምቦሳዋ
ከሞት ማደም ፍቅር ቻሪ ለሙት ቁርበት::
ከወተትዋ ኧሮንቅ ኧሮንቅ
አላቢዋም ፍንድቅ ፍንድቅ
ሲያታልላት ቂቂይ ዋሸ
በኩርማኑ ጨው መላሸ
አይ ላምነት የዋህነት እናትነት
ፍቅረ እናት እስከ ሲኦል እስከ ገነት::
ቁረንጮ ላሽ ላምነት ላሽ
ቆዳ ነካሽ::
ሳታውቅ አውነት
ነክሳ ቁርበት
ከረመች ስትታለል ስትታለብ
እንድታወርድ ለወተትዋ ስትቀለብ
ግን እኮ ብትሰረስረው
ከደረቀው ጅራቱ ስር ብትፈታታው
ትበላ ነበር ከጭዱ
ከሥጋው ከገለባው ከጉዱ:
ቋ ቋ ቋ

መቅደሴን

መቅደሴ ነሽ አንቺ፣ የዞትር አጣኝሽ፣ ካህንሽ ነኝ እኔ::
በመንበርሽ ዙሪያ እየወዘወዘ - - ብወረብ በቅኔ.....
ማነው ያጠነብኝ? ጠረንሽ አይደለም አይደለም ዕጣኔ::

ቋ ቋ ቋ

http://ethzare.wordpress.com

ይበለኝ

የኔ ገብስ ዛላ
«ማማ» ሳልሰራልሽ «ወንጭፌ» ሳይሰላ
«ወፍሽን» «አር». . ሳልል «ማሳየን» ሳላጥረው
ኑሮዬን ሳሰላ
ሳያሽሽ «መዳፌ» ታንቀህ ክረም ሲለኝ
ምርቅሽን ሳልከላ እፍ ሳልል ቅሜሽ
ይሄው እስከ ዛሬ ከትናጋዬ ነሽ።

ሕልም እልም

ነቃሁ ፤ ባነንኩ ፤ ህልሜን ነገርኳቸው።
«ህልም አልም» በል አሉኝ ፤ መፍታት ሲሳናቸው።
ከአልፍ አንቅልፋሞች ፤ ከስንት አልማጭ መሀል
- - - - ጉርብጥብጥ ጎዝጉዤ
በነቃሁበት ልክ ፤መልሼ ተጋደምኩ፤
ደግሞ ፍቹን ላልም ፤ ህልም አለሜን አለስኩ።

http://ethzare.wordpress.com


አዕምራ ለሔዋን

ሳይበርድሽ ስደርብ
ሳይሞቅሽ ላራግብ
እባብ ስሆን ርግብ
ስማስን የኖርኩት
የተንከራተትኩት
«ሀትምት ድንግል ነኝ ማንም ያላቀፈኝ» በማለትሽ ነበር::
ስጠብቅሽ የኖርኩ ስሸኝሽ እስከበር
. . . . . አኔም . . . . .
ያኔ ስጠጋሽ ስትጣጊኝ በእንቆቆ እንደማይሸር አቡይ ኮሶ
ስንማማል በአመብርሃን ስንገዘት በአምላክ ጦሶ
እንደ አንቺ የሥጋ ድር ባይኖረኝም የደም አውታር
ውላጤዬ ድንግል ነበር::
. . . እናም . . .
በዘመን ላይ ዘመን ደርቶ
የሠርጋችን ችቦ በርቶ
ጫጉላ ገባን ልንተያይ
በሔዋን ዓይን ልትወጋጊኝ በአዳም ዓይኔ ገላሽን ላይ::
ድምፁን ሰማን «አአምራ ለሔዋን» ን
ስትገሠሥ ድንግልና
ያች ለቅሶ ጥውም ቃና
ነጠላ ድበፅ አልፍ ዜማ
እስክ ገነት እስከ ራማ

አዲስ ምድር አዲስ ሰማይ
ልናንጋጥጥ ሽቅብ ልናይ
ሲደረመስ አዲስ ገደል አዛኝ ወጊ ጣፋጭ ቁስል
ትኩስ እንባ ወላፈን ጠል ጥፍር ሲሾል ወስፌ ሲግል
አኒያ አናትሽ ያባረሩኝ የዘጉብኝ
ሲያወድሱኝ ጀግና ሲሉኝ ብር አምባርሽ እንዲሰበር
ለደሙ ጨርቅ ሊቀነቀን ሲደነከር መስሎኝ ነበር:

- - - ሆኖም - - -
በጆሮዬ ተማፀንሽኝ ሰዘመናት ከደበቅሽኝ
ሕቡዕ ምስጢር አካፈልሽኝ
«አምጣ ምላጭ ሰንጢ ስጠኝ!
ደም ፍለጋ ጭኔን ቧጠኝ! የደም ጨርቁን ለውስልኝ»
. . . አልሸኝ . . .
አቱ ተይው . . . ውዴ እርሽው ስለ ፍቅሬ ሁሉ መልካም::
ቀድሞም ቢሆን ባንቺ መድማት እኔ አልረካም::
በሥጋ ሥሥ በደም አውታር ንፅህና አይለካም::
ተፍገምግሚ ተጥደፍድፊ
ክሱሪዬ ሰንጢ ልፊ
የራሴን ጭን በጥቻለሁ - - ደምሽን ከኔ ደምቻለሁ
ብር አምባሬን ሰብሬአለሁ የደም ሻሹን ነክሬአለሁ::
አቱ ተይው . . . ውዴ እርሽው ሁሉ መልካም::
ቀድሞም ቢሆን ባንቺ መድማት እኔ አልረካም::
በሥጋ ሥሥ በደም አውታር ንፅህና አይለካም::

http://ethzare.wordpress.com



(ጥቁር የበላይ የሆነባት ብቸኛዋ ሀገር ማኪያቶ ናት::)

ዕንባ ማኪያቶ

እስከሚዋሀዱ እስኪደባለቁ
ዘላዕሉ ፀላም አርሙን ከላይ ሆኖ
ቡና መቦረቁ
ያ ያልተዋጠለት ፀአዳው ወተቱ
ከታች ሆኖ ሽቅብ ቡናን መጋፋቱ
ብሔረ ማኪያቶ ሀገረ እንቶፈንቶ
ሀገረ ቀረርቶ
አንዳይኖር ሰላሟ ዘለዓለም ተናግቶ
ማንኪያ ፍቁረ ዕድ
ላይ ውጣ ታች ውረድ
ተፋጅተው ሳያልቁ አድርጋቸው ውሀድ::

የግጥም ጅምናዚየም

ቦርጫም ግጥሞች ሁላ እስኪያለከልኩ
ቅርፅ ምስጢራቸው እስኪገባ ልኩ፤
ለሆኑት ቀጫጫ ሰላላ መላላ
አልሚ ምግብ ህብር ቢሰጣቸውና ጎናቸው ቢሞላ፤
ዱብ ዱብ እንዲሉ እንዲቀበቀቡ፤
ለግልበት ብርዳቸው ሰምና ወርቅ ባዝሊን
ቀድመው እንዲቀቡ፤
ግጥም ጅም ታንያ ምናለ ቢገቡ::

http://ethzare.wordpress.com

የአፈ ጉባኤው መዶሻ

ይድረስ ለጉልያድ ውላጅ ዳዊት መስለኸኝ ለመረጥኩህ
መዝሙሬን ልትዘምርልኝ ዕንባዬን ልታነባልኝ
አኔነቴን ለወከልኩህ።
አዳሜ በአንተ ደነቀው ዕድሌ በአንተ ጨነቀው
አልፍ አጅ ሲንጫባረር አንቅልፍህን ስትሰልቀው።
ዳሩ ልብ ባልል ነው
ያ ሐዋርያ የለፈፈው
ለሮሜዎች የተጻፈው
ለውጭንቅር አለምሮህ መንደር በግልባጭ እንዲህ ይላል
«መዶሻ የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?
የሚያጸድቅ መዶሻ ነው የሚኮንንስ ማን ነው?
. . . . ይልቁንስ . . . . .
ጉልላታችን ያነፀው ካስማ ማገር ያፋቀረው
ወፍጮ ከመጅ የሚወቅረው በአፈ ጉባኤው ቀኝ ያለው
እኛን እኛን የሚወቅረው መዶሻው ነው።»
ያ የነገር ማሳረጊያ
ያ የርዕዮተ ዓለም ማፅደቂያ
ያ የልዩ ሐሳብ መድቂያ
የሚኮንን የሚያፀድቀው
የአፈ-ጉባኤው መዶሻ ነገር ቁጭት የሚያጠብቀው
ምናለ «ንቃ» ብሎ አናትክን ቢበጠርቀው።

(ፓርላማ ለሚያንቀላፉ «የሕዝብ እንደራሴዎች»)

ኩርኩም

አልፍ ኩርኩሞችን
የቀመሱ ራሶች
ዳሳሽ አጆች አንጂ
አይሹም ትራሶች።

1993 ዓ.ም

http://ethzare.wordpress.com

የገሀነም መዝገብ

አንድ ጠማር አንድ መዝገብ፣ አምልጦ ወድቆ ከሰማይ፣
ወደ ገሀነም የሚገቡ፣ ሰዎችን ዝርዝር የሚያሳይ፣
አነሳሁትና ስበር፣
ከራሴ ስም አስቀድሜ የፈለኩት ያንቺን ነበር።



ሉልነት? ሉሌነት?

ድንቄም አንድ መንደር
ሉሌነት ነው ትርፉ አንጉል መገደር
ሰለጠንን ስንል አንድ ጡት ተጣባን
ከመሀል አራዳ
ገዳመ ሉሌነት ለአርምሞ አለገባን
ከእናታችን ጓዳ አስቀረቀረብን
ሳናረጅ መንኩሰን ሳንፆም ቆረብን
አንድ መንደርነት ሉልነት የዋጁን
እንኳን ተጉራብተን በሩቁም አልበጁን!



http://ethzare.wordpress.com

የትኋን ሽቶ

ለፈንጣጣ ጣጣ
ፈውስ መድኃኒቱ ከመግል ከወጣ
ከትኋንም ሽቶ ማምረት ብንጀምር
ማንም ግድግዳውን አያስረጭም ነበር

አግቡኝ

እናንተ የቦዘናችሁ
እናንተ የተከዛችሁ
ቁመቀር ወፈት ’ሚሏችሁ
እናንተ ጋለሞታች ደናግል ጋለሞታዎች
ገደላችሁ ሥራ ፈቶ ከሚዞሩት አሞራዎች
ኑ . . . አኔ ልድፈነው ባለኝ በተሰጠኝ ዕቃ
መቼስ ጋብቻ ስሜት እንጂ ማደባለቅ አይደል ዕቃ::
አየነው አይደል ስንቱን ድብቅ ስሜቱን ወሽቆ
ተቀራርቦ በፈገግታ ተላልሶ ተሳስቆ
ተጣጥፎ ተፈራርሞ ተፈጣጥሞ ዕቃ ብቻ አደባልቆ
አየነው አይደል እንዴ ሰማኒያ ውሉን ቦጫጭቆ!
ኑ. . . ባንድ ጥላ እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል::
እንኳን ለሰባታችሁ
ለአልፍም እበቃለሁ::
አለኝ ጥሩ ማረሻ ሰርዶ የሚነቃቅል
ስርቻ ጉጡን መንግሎ ጭንጫ ላይም የሚያበቅል
ሸጥለሸጥ የሚያጨቀጭቅ ከምድረ በዳ ሚበቅል
እንደአላዛር ሞቶ ’ሚነሳ ስንኩፍ መግነዙን የሚያቀል
እርፍ ስሜቱ ሲነቀነቅ የሚተከል የሚነቀል
ተንጠልጥሎ የሚላጋ አለኝ ጥሩ ማረሻ
የእጦት ዝገት ነጥርቆት አጣ እንጂ ማባበሻ::
ኑ . . . ገደላችሁን ልረሰው ዳዋ አይብቀልበት
መቃብር አይሁንባችሁ ሀፍረትን ’ምትቀብሩበት
በጉራንጉር ጥጋጥጉ ማዕበል አይዝለልበት::
በጭቃ አሮንቃ አጎችሁ እሪያችሁ አይደንክርበት::
ፍቅር ከቆጠቆጠ ቅናት ካልለመጠጠው
የፍቅር ቡቃያ ጉጡን «የኢቲክስ» አረም ካልዋጠው
እንኳን ለሰባታችሁ ለአልፍም እበቃለሁ::
ሰው መቼም ነፃ ቢወጣ ከደዌ ሕመማት ቁጣ
በመደሰቻችን በኩል በታች ከመጣብን ጣጣ
ሰው መቼም ነፃ ቢወጣ ከሕግ ከምግባር ሰንሰለት
ቅድስና-ምንዝርና ትንሽ ምክንያት ጨምሮበት
እንደ ሰለሞን እንደ ዳዊት ለብዙ በበቃ ነበር
የፍቅር ነበልባሉ ግለት::

http://ethzare.wordpress.com

በሕልመ ሌሊት ቅዠቱ ተባብኦ ሲያዳክረው
ጀንዲውን አበስብሶ ትራስ ጭኑን ሲያሳቅፈው
ኮርማ መሆን የተመኘን አንግዴህ ምንጣፍ ይቁጠረው
. . . አ . . .
በኮርማ እንቅልፍ ስምጠት መሣል አረፍት አንጂ ግለት የለም
ኮርማ አውኑን ይኖራል አንጂ
ሕልም አለሙን አያቅፍም መቼም::
ኑ . . . ጣራዬ ሥር እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል::
ኑ . . . አግቡኝ ልሁን የጋራ
ሽለቋችሁን ልረሰው የጠበብቃችሁን ጋራ::
የቅናት የግለኝነት የስስት ውላጅ ባይወርሰው
መሠረቱ መሬት ነበር የዚያ የቀደመው ሰው
የቅናት የግለኝነት የስስት ጨቤ ባይምሰው
ሰው እኮ መሬት ነበረ ሁሉም በጋራ የሚያርሰው
በጠበቀው ባጠረው አይደል «መሬት እኮ ላራሹ ነው!!»
ፈጣሪ ቀድሞ ሲፈጥረው ሰው እኮ ድሮም መሬት ነው::
የሰው ልጅ የመሬት ሥሪት ዱድያሌብ ነው ከተባለ
የጋራ ሀዳድ አውጥተን አርሰን ብንዘራው ምናለ?
በአንድ ጋግርታም «ሞኖፓለ» ስሜቱ ከስሎ አያደረ
በአንድ ወታሻ ጥላ ስር ሥራ ስሩ ከደደረ
የስሜቱ አቦል ገንፍሎ ከሚሆን ዝቃጭ በረካ
ምናለ በሰብሰብ ጉልበት ለአንዲት አፍታ አንኳ ቢረካ?
ሰው አለኝ ማለት ከንቱ!
ደሀ ተሸጦ የማይገዛው ቅቅታም የተለተለው
ሊዝ ነው እንዴ እንደመሬቱ?
... መቼም...
የራሴ የግሌ ባዩ የሰው ልጅ ብልጠት ሲለካ
በሰለጠነ ቁጥር ቅናት ያጠቃዋል ለካ
ኑ . . . ጣራዬ ስር እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል::
ጉድለታችንን እንድፈን ቀዳዳችንን እንዝጋ ባለን በተሰጠን ዕቃ
መቼስ ጋብቻ ስሜትን እንጂ ማቀላቀል አይደል ዕቃ::
ኑ . . . እቴ ... ቱድመን እንንቃ
ስሜታችንን እንጂ ማቀላቀል ይቅር ዕቃ::

ጢም አልባ

ለቅንድብሽ ፀጉር ፀሐይ ሲጠልቅ አይቶ
ከንፈርሽ ሲቀባ እንዳንራብ ሰግቶ
የደቂቆች አምላክ አስቦ ለጊዜ
ጢምሽን አያበጠርሽ እንዳታይ አባዜ
ውበትን ሲያድልሽ ሲያደርግሽ ወሰባ
አገጭ ብቻ ሰጥቶ አረገሽ ጢም አልባ::

http://ethzare.wordpress.com

ብርሌ ሲነቃ

ብርጭቆ የዚች ጥቁር አፈር ግኝት
ባሕር ማዶ ስትሻገር
ሆንክ አሉ ማይክሮስኮፕ አጉሊ ነገር።
ከኛ ምድር እስክ ዛሬ - - አለህ ነገር ስንቀዳብህ
ጠጅ ስናንቆረቁር።
«ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ» ብሂሉ
የስንፍና መፈክራችን የጥበብ ጥበት ነው ቅሉ።
ብትነቃ እንኳ አትሆን ዕቃ፤
ስባሪህ ለምን ሊበቃ
ንቃትህስ ማንን ሊያነቃ
ብርጭቆ የስልጣኔውን ምስጢር።
ከኛ መንደር - - እኛ ሀገር - - ከኛ መንቆር
ሁሌ ጠጅ
ማ
ን
ቆ
ር
ቆ
ር

ልናነጋ ተኛን

ጨለማ ሲገዝፍ በቀን እኩይ ድርጊት
ዝንተ ዓለም ሳይናድ የጨለማ ምርጊት
በድሜጥሮስ ኩፋል «ቀን- ጨለማ» አያልን
ልንውል ተነስተን ልናነጋ ተኛን
በድሜጥሮስ ኩፋል
በገማ ጭንቅላት ጨለማ እየቆጠርን
እንደ ወፏ ሞረሽ በማያነጋ ድምፅ ሁሌ እየተብላላን
አንድ ቀን ላንውል ሦስት ሺ ዓመት ሞላን።

(ለኢትዮጵያ የሦስት ሺህ ዓመት ታሪክ)

http://ethzare.wordpress.com

አያቴ

«አክስኝ» ይላሉ ታከው ላይጠረቁ
«አቀፈኝ» ይላሉ እንደውሻ አፍንጫ
እየቀዘቀዙ ቆፈን እያጨቁ
እኔን አደንዝዘው ሙቀቴን ሊሞቁ
ደግሞ ብለው ብለው
ደግሞ እንደ ማሊያ
በሞት ዋዜማቸው
ያልበደለች ነፍሴን ይዘዋት ሊከንፉ
«ነፍስ እንለዋወጥ» ብለውኝ አረፉ::

ጉባኤ ፍና

በፅባሕ ተንሥኢ ብዕረ አዶዬ መባልና
አስመ ኢየሀልቅ ለነ ቅኔ ዘርዓ ሰብዕ ፍና::

አመበለት ብዕሬ
በጠዋት ተነሺ (እንበል ጉንበስ ቀና::)
የሰው ቅኔ መንገድ - ከቶ አያልቅምና!
(በኔው አረማመድ ባንቺ ጉንበስ ቀና)
(በጠዋት ተነሺ ሳይቀትር እንጓዝ በቅኔ ጉዳና::)

http://ethzare.wordpress.com

ኤዲት ይደረግ

በገብርኤል ሰይፍ ገማምሰን
የሰማይን ቅጥር ጥሰን
ኢዮር ራማን አስሰን
ፅርሐ አርያምን አምሰን
ካለበት ጉራንጉር ደርሰን
«አግዚአ-ብሔር» ቃሱን
ኤዲት አርገነው በመጣን::
ቀድሞስ «አግዚአ-አብ-ሔር» አንጂ
«አግዚአ-ብሔር» መች አጣን::

ሚዛኑ

እየተንገለልን- -እየተበጠርን
እየተነፈስን- - እየተነፋንም
አንዱን አሳንሶ አንዱን እየለካ
በራሱ ልኬታ ሲሰፍረን ቢኖርም
ቡሌት ዱቄታችን በቆጥና - ባጡ
ታችና ላይ ወርዶ ተንጋዶ ቢለካም
ሚዛኑ ዕድሜ ልኩን ራሱን አይለካም::

http://ethzare.wordpress.com

ከ'ኔ በጥቂቱ

ያ መፍጠሪያ ፍጡር ከአማልክት በታች
በጥቂት ባነሰ ተፈጥሮው ሳይረካ
ተፍጨርጭሮ ነበር አምላኩን ሊተካ።
ያ'ሁኑ ፍጡር ግን- - -
ከ'ኔ በጥቂቱ በመብለጡ ረካ።

አቤቱ

ሊተመንበር የወንበር አለታ
ስጠን።
ሊቀስብዕ - የለው አለታ
አታምጣ።
ሆዳችን ላይ ተቀምጦ
ጭንቅ- ላታችን ገረጣ።

http://ethzare.wordpress.com

ትበጥብህ?

ያች የተለጋች ጥንግ- - የተለጋች አሩር
የተለጋች እንቁር በገና ጫዋታ
አራሴን ስትነድለኝ ላፍታ በጨረፍታ
«እንትፍ» «እንትፍ» ብለው «ትበጥብህ» ሲሉኝ
በግዬ ነበረ በበደል ላይ በደል ያከሉብኝ መስሉኝ
- - - ብካስ- - - -
ወደውስጤ እንዳላብጥ
በሀሊና ቁጣ አቂሞ ቁስለቱ
መግሎ የሚከስመው
የላይኛው እበጥ ነበር መድኃኒቱ::

ቋ ቋ ቋ

ዘመነ መንሱት


ለዘመነ መንሱት
ለዚህ ጥቁር ቀኔ
መቼ ቦዘንኩ እኔ
ቦዘኔነቴንስ
አ...ደ...ገ...ኛ...ነ...ቴ...ን እጂቅርፎልኛል
ከሥራ አስገብቶ ያስወለውለኛል::

ቋ ቋ ቋ

http://ethzare.wordpress.com

ስለት

በስለት ፀንሰውኝ በስለት ወለዱኝ
በስለት አድጌ በስለት አለሁኝ
መጥፊያየም በስለት እንዳይሆን ሰግቼ
ሌላ ስለት ተሳልኩ ጧፍ ሻማ ገዝቼ።



የግብፅም ንጉስ አንዲቱ ሲፓራ
ሁለተኛይቱም ፉሐ የሚባሉትን
የዕብራውያንን አዋላጆች
አንዲህ ብሎ ተናገረ፡-
አናንተ የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ
ለመውለድ እንደ ደረሱ ባያችሁ ጊዜ
ወንድ ቢሆን ግደሉት ሴት ብትሆን ግን
በሕይወት ትኑር።
ዘፀአት 1፡-15

የወንድ ምጥ

አዋላጅቱ ሲፓራ ቃለ ፈጣሪን ዘንግታ፣ ቃለ ፈርኦንን ከሰማች፣
ፉሐም «ለአልል ዘጠኖ» አድልታ «አልል አስሩን» ካደማች፣
በፈርኦን ጠልሰመ መርገምት በእኩይ ኩፋሌሽ ተማምለው ሲዳዳሩ፣
ወላጆች ሊጨነግፉ «ለሴት አውል» ምጥ ካደሩ
ግሽር ዘረመል እንስቶችሽ ወንድ ማማጥ ካልተማሩ
አዋላጆችሽ እንስት አንጂ ወንድ ውሉድሽን ካልማሩ
ያለ እናቴ ካረገዝኩት ለአድርባይ አንስትሽ ተውላጥ
ወንድ ውሉድሽን «አህ!» ልበል
የውስጤ ሳንቃ ስኪነቃ የማህፀኔ በር አስኪላጥ።
የማህፀንሽ ፍሬ ዘሩ ገለባ አብቁን ለብቆ
ሆድሽ በፍልፈል ገፈት ሽርት ውሃ እርሾሽን አብቆ
ምድርሽ በጭንጋፍ አደፍ ገደልሽ በጭንጋፍ አትብት
ከተሞላ ውሎ አደረ።

http://ethzare.wordpress.com

ወላድ መሳይ ማህፀንሽ ላለማረጥ ሌላ አንቁላል ተበደረ፤
የፈርአንሽ እዋላጆች ሆዴ ሲገጥ ቅብ ፊታቸው ጠቋቆረ፤
በስደቴ ጨረቃሽ ዓይኑ ደም ቀላ ፀሐይሽ ፊቱ ጠቆረ::
. . . . አዬ እመት አፍሪቃ . . .
ዶሮሽ ተኝቶ አደረ፤ ጴጥሮስሽ አላስቀሰኩም::
የይሁዳሽ ፀፀት ዘግይቶ፤ ይሄው ዋይታዬ አልሰመረም::
ወንጭፌም የራሴን ክንድ አንጂ፤ጎልያድሽን አልሰበረም::
ምጤ ሽብዳ ሆኖ፤ ደንደላም ፀርሽን ካልወጋ፤
ሐሳቡ ወጋገን ሆኖ፤ ጠቋራ ሌትሽ ካልነጋ፤
ምኑ ላይ ነው እመት አፍሪቃ፤ የኔ በሥጋ መገለጥ፤
የሕልውናዬ ዋጋ?
ጥቁር አፈርሽን አቡክቶ፤ በራሱ አምሳል ሊሰራኝ፤
እስትንፋሱን አፍ ብሎ፤ «ሕልው-መዋቲ» ሲያደርገኝ፤
ጎርፌ እንዳልፍ ከሆነ፤ «ሕይወት-ሞት» ... በሚለው ስርጥ፤
ዋጋ ቢስ ነውና ጥንቱን፤ የኔ በሥጋ መገለጥ፤
ሥጋዬን አፈርሽን ውሰጅ፤ አሱም እስትንፋሱን ይዋጥ::
ጆሮሽ እዝነ አምላክ ሆኖ ቤተንግሥ ካልሽው ኩይሳሽ የምስጥ
ሹክሹክታን ቢያደምጥም
ለኔ ግን ታምቡሩን ቋጥኝ ይድፈነው ምጤን ፊትሽ አላምጥም::
ዘመነኞች ፉሐ ሰፓራሽ፤ አኒህ ባለምላጮቹ፤ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም::
ምጤን በሩቅ ሰሚ አንጂ፤ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፤
ጀግና ሲወለድ አይራሩም::
የሩፋኤል ፀበል ቂደርሽ ምጥ ያገላግል ነበር አሉ
ያኔ ዕንቁዕ ወላዶችሽ «እንኳን ማርያም ማረችሽ» ሲባሉ
አባክሽ ክቀድሞው ቂደርሽ እርጭኝ
በስማቸው ወኔዬ ይጋል
ለወንድ ምጤ ግልግል
በወንዶችሽ ስም ላስካካ::
በእነምኒልክ በእነሻካ፤
በአፍሪቃዊ የብዕር ፈርጥ በፀገመ ወሾይንካ::
የሞሮኮ ወራጅ ጅራት፤ ወይም ነጭ ምስጥሽ ይዘክር- - -
የሳሞሪ ቱሬን ነገር::
ሐኒባል፤ አብዱ ሙላህ፤ ሐቢብ ቦርጊዩባ፤ አብዱል ቃድር፤
የሊበያው የበረሀ አንበሳ፤ የምንለው አማር ሙክታር፤
ደግሞ ከኢትዮጵያ መንደር...
ኦሊቃ ድንግል፤ ኡመር ሰመተር፤

የወንድነትን ምስጢር፤
አፈርሽን እያሟጠጠ፤ ቀዩን ባሕር ከሚያወፍር፤
ግዮንሽ ቀለም ሆኖ፤ ታሪካቸውን ይዘክር::
እንደ አሳተ ገሞራ የሚፈልቅ፤ ሚያስጨነግፍ ዓይን ያለው፤
የደርቡሹን ሽርጥ ያስጣለው፤ የነጩን እናት ያስጠራው፤
የምጽዋችን የአሳት በር፤ አሉላ አባ ነጋ አኮ ነው::
የአጼ ቴድሮስ አቤልሽም፤ መቅደላ የፈሰሰ ደሙ፤
ይሄው አስክ አሁን ይጮኻል፤ ሰሚ አድማጭ ላጣ ወንድሙ::
የኔ ኢየሱስ ቴድሮስ...
ደሙን ቢያፈስልኝም፤ ሥጋውን ቢቆርስልኝም
አልቀረብኩበትምና፤ ይሄው ወንድነት የለኝም::
ሞትን ከእንቅልፍ ያሳነሱት፤ ቅዱሱ አቡነ ጴጥሮስ፤
ሞት አልቀምስም ብለው ነበር፤ ውዳሴ ማርያም ሳላደርስ::
የሸንቁጥ ልጆች፤ አብዲሳ አጋ... በኢመዋቲ ነፍስ ወሥጋ
ሰማይ ቅጥርሽ አይችለውም የከፈሉልኝን ዋጋ::
. . . . ሆኖም . . . .
ያሁኖቹ ፉሐ ሲፓራሽ፤ አኒህ ባለምላጮቹ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ሰሚ አንጂ፤ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፤
ጀግና ሲወለድ አይራሩም::
. . . አየ እመት አፍሪቃ . . .
ምጥ ግልግሌን አይ ብዬ አንጂ ጸሎቴ እንዲህ መብዛቱ
ክንፋም ሰይጣንሽን ፈርቼ አንጂ፤ ምህላዬ መበርከቱ
ጠሚን እንዳላድር አንጂ፤ ሳይኖረኝ ምሳል በከንቱ
ፈጣሪሽ ሞኝ አይደለም፤ ፍቅሩ አንበርክኮ ካልገዛኝ፤
ሲኦል ገሐነሙን ፈርቼ፤ አምላኬ አምላኬ ካልኩኝ፤
እንጦርጦስ አንጂ ትርፌ፤ አውቃለሁ እንደማይምረኝ::
በምድርሽ አንድ አምላክ በዝቶ ፈጣሪሽ ዝም አለ ምነው?
ዋርካሽ የሰይጣን ማደሪያ፤ ተራራሽ ቤተ ጸሎት ነው::
ሁሉ ጸሎተኛ አንጂ፤ ቀድሞ አዳምን እንዳዘዘው፤
ምድርሽን የሚቆፍር ማነው?
ምድራዊ መናሽ ላይ ቆሞ፤ የህዝብሽ ልቡ እዛ! ነው::
ክርስቲያንሽ ኢየሩሳሌም ሙስሊምሽ መካ መዲና ወጣትሽ
ባሕር ማዶ ነው::
. . . . አዬ እመት አፍሪቃ . . .
እርጉዝ አይሽተው የለ
ይሽው ሳምጥ ሽተተኝ ከምጤ ጸዕር የከፋ

http://ethzare.wordpress.com

ከዳርቃር የማሽላ ገንፎ፣በግመል ሽንት ሲገነፋ፣
ሞቃዲሾ ሰይፏ ሲቀላ፣ ደም እንደ ውሃ ሲደፋ
ይህን የትውልድ ጉግ ማንጉግ፣ ይህን የመከራ አዳፋ፣
የማያገላብጥ መንሽ፣ ጉዱን የማይዝቅ አካፋ፣
ለትውልዱ ጋሬጣ ሳይሆን፣ ወዲያ ይሰባበር ይጥፋ::
ምሁር ያልሸው በቀቀንሽም፣ ቅጥርሽን ሲሻገርም፣
ግብረ ሰዶምን እንጂ፣ ሌላ ተምሮ አይመጣም::
ምነዋ እመት አፍሪቃ፣ ለምለምሽ ሆነ አሜከላ
እስከ መቼ ጠጠርሽን ልልቀም፣ የማይሞላ መጥቅሽን ላስላ?
እረኛሽ በጉን አያውቅም፣ ፀናብን የራሱ ዱላ::
የበግ ግዳዩን እየጣለ፣ ይፎክራል ብሎ ተኩላ::
በግን ከተኩላ ሊያፋቅር፣ ከነጫነጭባች ምድር፣
እርግብ ነኝ ብሎ ሲበር፣ ያስታርቅ መስሎ ሲያናቁር፣
ደጉ የሐገሬ ቁራ፣ ታዝቦ ነበር ዛፍሽ ሥር::
አፍሪቃ ያንቺ የጥፋት ውሃ፣ ይሄው እስከ አሁን
አልጎደለም::
ፈጣሪሽ ቀስቱን መልሶ፣ ቃልኪዳን አልገባልሽም::
ቁራሽ ይቆርጠው ቄጤማ፣ ያርፍበት ምድር የለሽም::
ሰላም በሌለበት አቅራርቶ፣ ቁራሽ እንደ ርግብ
አይዋሽም::
ወትሮም ቁራ ቁራ እንጂ፣ ደግ መላይ ግርብ አይደለም::
. . . አዬ እመት አፍሪቃ . . .
ያሁኖቹ ፉሐ ሲፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ስሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ ጀግና ሲወለድ
አይራሩም::
አያቶቻችን ጥንትም፣ ወሬ መጠረቅ ያውቃሉ::
የጭራቅ ተረት ነግረውን፣ ይሄው በፈሪ ተሞልቷል፣ ጓዳ
ጎድጓዳሽ ሁሉ::
አባቴም ተረት ሲተረትር፣ እንዲህ እንዲያ ሊያለ ነበር::
ታዲያ ምን ነካሽ አንቺ ምድር አንቲ አጓለ ማውታ
እንዳልነበርሽ የጥጋብ በር...
እንዴት ከቋትሽ አመድ፣ ከጎታሽ ግርድ ይከመር?
የአውድማሽ ምርት ተትረፍርፎ፣ አለሌች ውድን ሲጫኑ
አሀዮችሽ ግርዱን ንቀው፣ ከምርቱ እንዳል ዘገኑ፣
ገለባ ብቻ ከምሬ፣ በሬ ለጉሜ ወቅቼ፣
ፍሬ አልባ አብቄን እፍ ስል፣ እስትንፋስ እንኳ አጥቼ፣

ስሄድ አያየሽ ዝም አልሽኝ፣ ስልቻዬን ግርድ ሞልቼ::
እንጀራ በቅርጫት ተግዞ፣ ግብር አውራጅ ተሰርቶ
እንዳልተበላ ከፊትሽ፣ የሱሪ ሽምቀቅ ተፈቶ፣
ዝም እንዳላሉ ውሾች፣ ድመቶች ካፋቸው ሲበሉ፣
አሞራች ጠግበው ከሰማይ፣ የሥጋ ቁራጭ እንዳልጣሉ፣
ጥንብ አንሳው እንኳን፣ ጥንብ ንቆ
አንዳል ሞላ ከረጢቱን፣ ከምርጥ ሥጋሽ ጠርንቆ
እኔ.. የግዮን ደለል፣ የጀማ ፏፏቴ አረፋ
እኔ.. የአያቶቼ ግርድ፣ የዘመን ውሽንፍር ዳፋ
እኔ.. የክሊማንጃሮ አውሎ፣ የኮንጎ አለሌ ፋጉሎ፣
እኔ.. የ«ኬፕ ኦፍ ጉድሆፕ»... «ባድሆፕ»...
እኔ.. የቪክቶሪያ አምባዛ...የዛዬር የቀትር ጤዛ...
እያኗኗርኩ ለኑባሬ
ቆሎ በቆኮርኪ ሰፍሬ
እንጀራ በላስቲክ ገዝቼ፣ የሳሳ እንደላስቲኩ፣
የጓያ ወጤን ወጥውጬ፣ ከመማይ ቀጭን በልኩ፣
እንጀራዬ ከወጤ ቀድሞ፣ መሶቤ ወዲያው ሲራቆት፣
በወጤ አውጥበት ሳጣ፣ ወጤን በወጤ ዋጥኩት::
. . . . ታዲያ ይህ በዚህ ሳይበቃ . . . .
ያሁኖቹ ፉሐ ሲፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ፣ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ስሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፣
ጀግና ሲወለድ አይራሩም
ጢማም ሽመግሌዎችሽ፣ ከዳካር አስከ ኤደን በር፣
ከፖርት ኤልዛቤጥ ደቡብ ጫፍ፣ አስከ ፎኒሽያን ምድር፣
አርግማናቸው እንጂ፣ ምርቃታቸው አይሰምር::
ለጣዖታቸው ስታረድ፣ የዓዕር ድምፄ ሲወጣ፣
ሕጻን ልጃቸው እንዳይሞት፣ በፍርሃት ነፍሱ እንዳትወጣ፣
ትልቅ ከበሮ አስለጉመው፣ ይደልቅ ነበር ባለ ዕጣ::
እኩይ ጠንቋዮችሽም አፍዝዝ፣ አደንግዝ፣ አቅዝዝ አፈርዝዝ
መተታቸው እንጂ... መስተፋቅር፣ መስተጻምር፣ መፍትሔ
ሥራያቸው አይሰራም::
እኔም ምጤን አገላገል ስል፣ ለዛየርሽ ዳንግሌ በጌን፣ ለግዮንሽ
ቀይ ዶሮ አላርድም፣
ለደም መጣጭ አጋንንቶችሽ፣ ወርካሽ ሥር እጀን አልፀፋም::
አዎ እኮሰኩስላለሁ፣ አሁን አባ ጨጓሬሽ ነኝ::
ድምፄ በራማ ተሰምቶ፣ ክንፎቼን ከመለስልኝ፣

http://ethzare.wordpress.com

ያኔ ቢራቢሮ ስሆን ነው ንበሮ ክበር ምትይኝ፣::
ያኔ...ሌለኛ አበባችዎሽ፣ በቀለማቸው ቢበስቡኝ፣
እነሱን አላዳቅልም... «ቱ!» ወለላቸው ይቅርብኝ::
ወንድነቴ ቅርናት ከሆነኝሽ፣ በከንቱ ካንጠለጠልኩት፣
ብልቴን እርኩሰት ቆርጠ፣ «ብር አምባሩን» ይስበርበት::
ምጥ ግልግሌ ቀርቶ እንኳ፣ ጩኸቴ ብስናት ከሆነኝሽ፣
የማይጠረቃ ሞትሽ ይውሰደኝ፣ አቁማዳ ከርሱ ይሙላልሽ
አጥንቴን ጅብሽ ቆርጥሞ፣ ጥንብ አህያሽን ይብላልሽ::
እንዲህ አይደል «ወንድ» ሲማጥ
ሲጨላልም ሲደጓጉን አርያሬስ ስኑ ሲቀልጥ
በዮቶር የነባነት ቃል እንደሙሴ እንዲያሻግር
ሽሽግ አርገው በግዮን ስር . . .
እንዲህ አይደል «ወንድ» ሲማጥ «እም» የሚያለኝ የሚያናግር::

ꕥ ꕥ ꕥ

«.....ወንዶችን ሕጻናትስ ለምን አዳናችሁ?.....»
«የዕብራውያን ሴቶች እንደ ግብጥ ሴቶች ስላልሆኑ...አዋላጆች ሳይገቡ ስለሚወልዱ ነው::»
ዘፀአት 1፡ 18

http://ethzare.wordpress.com









የይስማዕከን ግጥሞች ስቀምሳቸው እንደ ግጥም ዐለላ መጣፈኛም ብቻ ሳይሆን፣ እንደቅኔ ወይን ለማስከር ይዳርቸዋል'ኮ! አባቱ ይመትቸ የኔ ወይን የመድኃኒም ዓቅም ማነስ ይሆን? ለነገሩ ቅኔውን ከየት "ዘረፈው?" በሉ። ግያሌችሁም እነደወገኖቹ በቅሎ ራሳት ዓበብ መዘረፍ ዓመል ሳይሠንበት አልቀረም። አቦ አሁንም በዘረፈ! አለበለዚያ ይህ ልጅ ለቅኔ "ቅልውጭ" ወደ ዋሸራ ብቅ ብሎ ይሆን? ወይስ በእንግድነት ተጋብዞ ከዋሸራ የቅኔ ማዕድ ታድሞ የተቋደሰውን ለእኛም ሊያቋድሰን ቅንጥር አመጣልን? ዘሩ ይለምልም!

ይስማዕከ እንዘቃቅላ ገላጊ ነው። የግጥሞቹ ፍሬዎች ግን ከእንዘቃቅላ ምጣብና ከልጅ ልቦና የተፈለፈሉ አይመስሉም። በሰብአዊ ገጠመኞች የበለጸገ ሰው የሚያንበለበላቸው የስሜት ወላፈኖች ናቸው ስል ስመ አምላክ ጠርቼ አመሰከራለሁ። የግጥም "ክዳኑን ያውጣችሁ" ብያቸዋለሁ፤ ዚስ እዳያይብኝ። "ክዳኑን ያውጣችሁ" ስል መርቴም ለእናንተ ለአንባቢያን [illegible] ሀ.ኮቪ.ንም አንደሚወዳቸው ውቃቤዬ ይነግረኛል።

[illegible] ያመለክታሉ። ባዛሩ የእኛን ክቡክቤ የሚሻ የጎበዝ ነፍስ [illegible] ስለሆነም ይቺን የወለዳትን የበኩር ልጄን ስማችሁት እማዋ የላኮ ዚ አንዲያስገኝ አሁንም "በደባብ ሂድ" በሉልኝ፤ አፈር ስሆን!

የሻው ተሰማ የኩባው

DFB
D AMH Yis
Yismake Werku
Yewend mit 2010
dfb m 2
03011126467002

http://ethzare.wordpress.com